«የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት፣ በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» 2ጢሞ. 3፥16-17



«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)፥130


Global Good News Literature
የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
P.O.BOX 451336
Los Angeles, CA 90045
email: info@globalgoodnews.org


Copyright © 2008




## ማውጫ

### ክፍል ፪


| | ገጽ |
|---|---|
| ትምህርት ሰባት፡- የቤተ ክርስቲያን ሥርዐቶች ................................ | 5 |
| ቅዱስ ቍርባን ................................................................ | 5 |
| ፩ የቅዱስ ቍርባን ሥርዐት ዐላማ ....................................... | 5 |
| ፪. የጌታን እራት ሥርዐት ስንት ጊዜ መፈጸም አለብን? ........ | 5 |
| ፫. ኅብስቱ (እንጀራው) ምንን ያመለክታል? ......................... | 5 |
| ፬ ጽዋው (ወይኑ) ምንን ያመለክታል? ................................. | 6 |
| ፭. በቅዱስ ቍርባን መሳተፍ ያለበት ማን ነው? ..................... | 6 |
| ፮. በቅዱስ ቍርባን ለመሳተፍ አንድ አማኝ ምን ማድረግ አለበት? | 6 |
| ፯. በቅዱስ ቍርባን መሳተፍ ያለብን በሁለት ምክንያቶች ነው ......... | 7 |
| ጥምቀት ................................................................................... | 7 |
| እነዚህ ልዩ ልዩ የጥምቀት ዐይነቶች ምንድን ናቸው? .................. | 7 |
| 1. መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አካል ውስጥ ሲያጠምቀን ........... | 8 |
| 2. የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ............................................ | 8 |
| 3. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ................................................ | 9 |
| 4. የመከራ ጥምቀት ......................................................... | 10 |
| 5. የውሃ ጥምቀት (ኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ ሁሉ እንዲጠመቅ ያዘዘው) ......................................................... | 10 |
| ትምህርት ሰባት፡- የቤተ ክርስቲያን ሥርዐቶች - ጥያቄዎች ................ | 16 |

## የወንጌል ሥነ ጽሑፍ አገልግሎት
## የመላላክ ትምህርት

የዚህ የመላላክ ትምህርት ዋና ዐላማ በጌታ ዐዲስ ለሆኑ፣ እንዲሁም በጌታ ከሆኑ ቈየት ቢሉም፣ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን የበለጠ ለማጠናከር ለሚፈልጉ ወንድሞችና እኅቶች መሠረታዊ የሆኑትን ክርስቲያናዊ ትምህርቶች ለማስተማርና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እንዲያድጉ መርዳት ነው። «ፈረስን ወደ ውሃ ታመጣዋለህ እንጂ እንዲጠጣ አታስገድደውም» እንደሚባለው ሁሉ፣ እነዚህ ትምህርቶች ተማሪው በትጋት ካልተከታተላቸውና በውስጣቸው ያሉትንም ጥቅሶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እያመሳከረ በሚገባ ካላጠና፣ እንዲሁ በአንድ ጊዜ ንባብ ብቻ የሚፈለገውን ውጤት ያስገኛሉ ማለት አዳጋች ነው። ስለዚህ ይህንን ትምህርት የምትከታተሉትን ሁሉ፣ እያንዳንዱን ትምህርት መጽሐፍ ቅዱሳችሁን አውጥታችሁ ጥቅሶቹን በማመሳከር በትጋት፣ እንድታጠኑት እናበረታታለን።

እነዚህን ትምህርቶች በግልም ሆነ በኅብረት መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ላይ መጠቀም ይቻላል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጀማሪዎችን የማስተማር ኀላፊነት ያለበት ሰውም ሌሎችን ለማስተማር ሊጠቀምባቸው ይችላል። ትምህርቶቹን በእኛ በኩል በግል ለመከታተል የምትፈልጉ ግን በመጀመሪያ መመዝገብና የመታወቂያ ቍጥር መቀበል ይኖርባችኋል። ከዚያም ከእያንዳንዱ ትምህርት መጨረሻ ላይ ላሉት ጥያቄዎች በቂ መልስ በመላክ የመላላኩን ትምህርት መቀጠል ትችላላችሁ።

የመላላክ ትምህርቱ፣ ዐሥራ ሁለት መሠረታዊ የሆኑ ትምህርቶችን ያካተተ ሲሆን፣ አራት አራቱን ከፋፍለን በሦስት ክፍሎች አቅርበናቸዋል። አርእስቱ፣ ለአንድ ክርስቲያን ያስፈልጋሉ ብለን ያመንባቸው አርእስት ናቸው። ትምህርቶቹን በጥሞናና በረጋ መንፈስ አጥንታችሁ ከትምህርቱ ጋር የተገናዘበ በቂ መልስ እንጂ በችኰላ የቸልተኝነት ወይም ከትምህርቱ ጋር የማይዛመድ መልስ እንዳትሰጡ ልናሳስብ እንወዳለን።

ትምህርቶቹን በደንብ አጥንታችሁ የጥያቄዎቹን መልስ፣ በየክፍሉ ያሉትን አራት አራት ትምህርቶች በየተራ፣ ወይም የዐሥራ ሁለቱንም ትምህርቶች በአንድነት ስትልኩልን፣ መልሳችሁን አይተን ይህንን የመላላክ ትምህርት እንደ ጨረሳችሁ የሚገልጽ የምስክር ወረቀትና ትራንስክሪፕት እንልክላችኋለን።





# ክፍል ፩



**«የቃልህ ፍቺ ያበራል፤
ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።»
መዝ. 118(119)÷130**

## ትምህርት ሰባት፡- የቤተ ክርስቲያን ሥርዐቶች

የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤተ ክርስቲያን የሰጣቸው ሁለት ሥርዐቶች አሉ፤ እነርሱም ቅዱስ ቍርባንና የውሃ ጥምቀት ናቸው፡፡ ሥርዐት በአንድ ባለ ሥልጣን የተደነገገ ሕግ ወይም ትእዛዝ ማለት ነው፡፡

### ቅዱስ ቍርባን

ቅዱስ ቍርባን በመባል የሚታወቀው የቤተ ክርስቲያን ሥርዐት አንዳንድ ጊዜ «የጌታ እራት» ተብሎም ይጠራል፡፡ ይህም ጌታችን ከመሰቀሉ በፊት ከደቀ መዛሙርቱ ጋር የተካፈለውን የመጨረሻ እራት የሚያመለክት ነው፡፡

ቃሉ እንዲህ ይላል፤ «ጌታ ኢየሱስ ዐልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፤ ቈርሶም፣ «እንካችሁ ብሉ፣ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» አለ፡፡ እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን አንሥቶ፣ «ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን ዐዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ፡፡ ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራችሁና፡፡» (1ቆሮ. 11፥23-26)

### ፩ የቅዱስ ቍርባን ሥርዐት ዐላማ

1. የክርስቶስን ሞት ለማስታወስ (1ቆሮ. 11፥26)፣
2. ከሌሎች አማኞች ጋር ያለንን አንድነትና ኅብረት ለመግለጽ ሉቃ. 22፥14-20፤ 1ቆሮ. 10፥21፤ 11፥23-26)፣
3. ለጌታ ኢየሱስ ያለንን ታዛዥነት ለመግለጽ፣
4. ክርስቶስ ተመልሶ እንደሚመጣ ለማሳሰብ (1ቆሮ. 11፥26)፡፡

### ፪. የጌታን እራት ሥርዐት ስንት ጊዜ መፈጸም አለብን?

አማኞች የጌታን እራት ሥርዐት በሚፈልጉበት ጊዜ ሁሉ ሊፈጽሙት ይችላሉ፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ የተወሰነ ጊዜ ተጠቅሶ አንመለከትም፡፡

### ፫. ኅብስቱ (እንጀራው) ምንን ያመለክታል?

«… እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፡፡» (1ቆሮ. 11፥23-24) ብሎ ጌታ ኢየሱስ ስለ ተናገረ ኅብስቱ የኢየሱስ ሥጋ ምሳሌ ነው፡፡





### የጌታ ሥጋ ለእኛ የተቈረሰው እንዴት ነው?

ሀ. ጐኑ በጦር ተወጋ (ዮሐ. 19፥34)፡፡

ለ. በጲላጦስ ተገረፈ ዮሐ. 19፥1 «በመገረፉ ቍስል ተፈወሳችሁ» (ኢሳ. 53፥5፤ 1ጴጥ. 2፥24)፡፡

ሐ. ወታደሮቹ የእሾህ አክሊል ጐንጕነው አደረጉለት፤ ዘበቱበት፤ ተፉበት፤ ራሱንም በመቃ መቱት (ማቴ. 27፥28-31፤ ማር. 15፥17-20)፡፡

### ፬ ጽዋው (ወይኑ) ምንን ያመለክታል?

«ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፤ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኀጢአት ይቅርታ የሚፈስ የዐዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡» (ማቴ. 26፤ 27-28፤ ዕብ. 9፥19)

ከዚህ ጥቅስ እንደምንረዳው ወይኑ የሚያመለክተው፣ ስለ ኀጢአታችን የፈሰሰልንን የኢየሱስ ክርስቶስን ደም ነው፡፡ የኀጢአ ትን ይቅርታ ወይም ስርየት የምንቀበለው፣ የነበረብን የኀጢአት ዕዳ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ሲሻርልንና ነጻ ስንሆን ነው፡፡ በ1ዮሐ. 1፥7፣ «የልጁ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኀጢአት ሁሉ ያነጻናል፡፡» የሚለው ስለዚህ ነው፡፡

### ፭. በቅዱስ ቍርባን መሳተፍ ያለበት ማን ነው?

«ጌታ ሥጋው እስኪቈስል፣ ደሙም እስኪፈስስ ድረስ ራሱን አሳልፎ የሰጠው ለእኔ ሲል ነው» ብሎ በጌታ በኢየሱስ የሚያምን እውነተኛ አማኝ ሁሉ መሳተፍ ይችላል (1ቆሮ. 11፥24)፡፡

### ፮. በቅዱስ ቍርባን ለመሳተፍ አንድ አማኝ ምን ማድረግ አለበት?

ራሱን መመርመር አለበት፤ ልባችንን መርምረን ኀሊናችን በአንዳች ነገር የሚወቅሠን ከሆነ፣ መጀመሪያ ያንን ነገር ማስተካከል አለብን፡፡ የምናስተካክለውም ንስሓ በመግባት ነው (1ቆሮ. 11፥27-32)፡፡ «በኀጢአታችን ብንናዘዝ ኀጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዐመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡» (1ዮሐ. 1፥9)

«ማንም ሰው ያልተገባው ሆኖ ሳለ የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታንም ጽዋ ቢጠጣ፣ በጌታ ሥጋና ደም ባለዕዳ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው ይህን ኅብስት ከመብላቱና ይህንንም ጽዋ ከመጠጣቱ በፊት ራሱን መመርመር አለበት፡፡ ማንም ሰው የጌታ ሥጋ ምን መሆኑን ለይቶ ሳያውቅ የጌታን ኅብስት ቢበላና የጌታን ጽዋ ቢጠጣ በራሱ ላይ ፍርድን ያመጣል፡፡» (1ቆሮ. 11፥27-29 ዐዲሱ ትርጕም)

## ፯. በቅዱስ ቍርባን መሳተፍ ያለብን በሁለት ምክንያቶች ነው

ሀ. ጌታ ያደረገልንን እንዳንረሳ፤ «ይህንን ለመታሰቢያዬ አድርጉት፡፡» (1ቆሮ. 11÷25)፡፡

ለ. ኢየሱስ እስከሚመጣ ድረስ ሞቱን (ስለ ኀጢአታችን እንደ ሞተ) ለመናገር (1ቆሮ. 11÷26)፡፡

እግዚአብሔር የሰዎችን ዝንጉነት ስለሚያውቅ፣ ጌታ ያደረገልንን ውለታ እንደ እስራኤላውያን እንዳንረሳ አዘዘን፤ «ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና፡፡»

የጌታን እራት በምንወስድበት ጊዜ ሁሉ ልቦናችን ዘወትር ለእኛ በፈሰሰው ደሙና በቈሰለው ሥጋው ላይ ይሁን፡፡

## ጥምቀት

ጥምቀት ማለት በአንድ ነገር ውስጥ መግባት፣ መነከር፣ መጥለቅ ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ልዩ ልዩ የጥምቀት ዐይነቶች እንዳሉ እናያለን፡፡

«ስለዚህ የክርስቶስን ነገር መጀመሪያ የሚናገረውን ቃል ትተን ወደ ፍጻሜ እንሂድ፤ መሠረትን ደግመን አንመሥርት፤ እርሱም ከሞተ ሥራ ንስሓና በእግዚአብሔር እምነት፣ ስለ ጥምቀቶችና እጆችንም ስለ መጫን፣ ስለ ሙታንም ትንሣኤ፣ ስለ ዘላለም ፍርድም ትምህርት ነው፡፡» (ዕብ. 6÷1-2)

### እነዚህ ልዩ ልዩ የጥምቀት ዐይነቶች ምንድን ናቸው?

1. **መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አካል ውስጥ ሲያጠምቀን**

ይህ ጥምቀት አንድ ሰው ንስሓ ገብቶ በኢየሱስ ክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ በቅጽበት መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አካል ውስጥ የሚያጠምቀው (የሚያስገባው) ማለት ነው፡፡

«አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ (በመንፈስ ቅዱስ) አንድ አካል (የክርስቶስ አካል) እንድንሆን ተጠምቀናልና፡፡ ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል፡፡ (1ቆሮ. 12÷13)

ይህ ጥቅስ በውሃ ውስጥ ስለ መጠመቅ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት በክርስቶስ አካል ውስጥ ስለ መጠመቅ (ስለ መግባት) ነው የሚናገረው፡፡ አጥማቂው መንፈስ ቅዱስ ነው የምንጠመቀውም በክርስቶስ አካል ውስጥ ነው፡፡ ከዚያች ቅጽበት ጀምሮ በክርስቶስ አካል ውስጥ አንድ ብልት እንሆናለን ማለት ነው፡፡ 1ቆሮንቶስ ምዕ. 12ን በሙሉ





ስናነብ የሚናገረው ስለ ክርስቶስ አካል እንደ ሆነ እናስተውላለን፡፡ «ተጠ ምቀናል» የሚለውንም ቃል ከአጠቃላይ ከምዕራፉ ሐሳብ ጋር ማያያዝ አለብን፡፡

በገላ. 3÷27 ላይም የተገለጸው ጥምቀት ይህ ጥምቀት ነው፡፡ «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ (በእርሱ አካል ውስጥ ትሆኑ ዘንድ) የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል፡፡» አንድ ሰው ክርስቶስን የሚለብሰው መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አካል ውስጥ ሲያጠምቀው ነው፡፡

በኤፌሶን 4÷4-5 ላይ «አንዲት ጥምቀት» ተብላ የተጠራችው ጥምቀት ይህች ጥምቀት ናት፡፡ «በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ፤ አንድ ሃይማኖት (እምነት)፣ አንዲት ጥምቀት፣ ከሁሉ በላይ የሚሆን፣ በሁሉም የሚሠራ፣ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ፡፡»

አንድ ኀጢአተኛ በንስሓ ወደ እግዚአብሔር ተመልሶ በክርስቶስ ኢየሱስ አካል ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ሲጠመቅ፣ አንዲት ጥምቀት የተባለችውን ይችን ጥምቀት ፈጸመ ማለት ነው፡፡

2. **የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት**

«ለኀጢአት ስርየት የንስሓን ጥምቀት እየሰበከ በዮርዳኖስ ዙሪያ ወዳለችው አገር ሁሉ መጣ፡፡» (ሉቃ. 3÷3)

የዮሐንስ መጥምቁ ጥምቀት ሰዎችን ለሚመጣው መሲሕ (ለኢየሱስ ክርስቶስ) የሚያዘጋጅ የንስሓ ጥምቀት ነበረ፡፡ ይህ ጥምቀት የተጀመረውም ሆነ ያከተመው በመጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎት ነው፡፡ ለመሲሑ መምጣት ዝግጅት ለዚያን ዘመን ብቻ በዮሐንስ አገልግሎት የተፈጸመ የጥምቀት ሥርዐት ነበር፡፡

3. **የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት**

ይህ ጥምቀት ክርስቶስ ኢየሱስን የተቀበለ አንድ አማኝ ሊቀበለው የሚችለው የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ወይም ጥምቀት ነው፡፡

«እኔስ ለንስሓ በውሃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፡፡» (ማቴ. 3÷11)

«አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ፡፡» (ሐዋ. 1÷5)፡፡

ይህ ጥምቀት በቍጥር አንድ ላይ ካለው ጥምቀት የሚለየው፣ በቍጥር አንድ ላይ አጥማቂው መንፈስ ቅዱስ፣ የምንጠመቀው ደግሞ በክርስቶስ አካል ውስጥ ሲሆን፣ ይህኛው ጥምቀት ግን አጥማቂው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሆን፣ የምንጠመቀው (የምንሞላው) ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ «እርሱ (ኢየሱስ ክርስቶስ) በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠ ምቃችኋል፡፡»

## 4. <u>የመከራ ጥምቀት</u>

ይህ ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ሊቀበለው ስላለው መከራ ሲናገር በተጠቀመበት አነጋገር የጠቀሰው ጥምቀት ነው።

«ነገር ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ፤ እስክትፈጸም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ?» (ሉቃ. 12፥50)

«እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ፣ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን?» (ማቴ. 20፥22)

## 5. <u>የውሃ ጥምቀት</u> (<u>ኢየሱስ ክርስቶስ አማኝ ሁሉ እንዲጠመቅ ያዘዘው</u>)

ይህ ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ ሐዋርያት እንዲፈጽሙት ያዘዘው የውሃ ጥምቀት ነው።

«እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ <u>በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣</u> ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው።» (ማቴ. 28፥19)

ይህኛው ጥምቀት እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት ለኀጢአት ስርየት የሚፈጸም የንስሓ ጥምቀት ሳይሆን፣ ንስሓ ገብቶ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነ ሰው ሁሉ ሊፈጽመው የሚገባ፣ የክርስቶስ መሆናችንን የምንመሰክርበት ጥምቀት ነው።

## <u>የዚህ ጥምቀት ትርጒም ምንድን ነው?</u>

### ሀ. ከክርስቶስ ጋር ያለንን ኅብረት ያመለክታል።

ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ ሞተ በመንፈስ ግን ሕያው እንደ ሆነ አንድ አማኝም፣ «ለኀጢአትና ለዚህች ዓለም ሞቻለሁ፤ በመንፈስ ግን ለክርስቶስ በሕይወት እኖራለሁ ብሎ የሚመሰክርበት መንገድ ነው። ወደ ውሃው ሲገባ፣ «ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ውስጥ እንደ ገባ ከክርስቶስ ጋር አብሬ ተቀብሬአለሁ» ማለቱ ሲሆን፣ ከውሃ ውስጥ ሲወጣ ደግሞ፣ «ክርስቶስ ከመቃብር እንደ ተነሣ እኔም በዐዲስ ሕይወት ለክርስቶስ ለመኖር ከክርስቶስ ጋር ተነሥቻለሁ» ማለቱ ነው።

«ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በዐዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፣ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን። ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን፣ <u>ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን</u>።» (ሮሜ 6፥3-5)

<u>«በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፤ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር አሠራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ</u>።» (ቆላ 2፥12)





### ለ. <u>የበጎ ኅሊና ልመና ነው።</u>

«ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውሃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፣ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህም ውሃ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል፤ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፤ <u>ለእግዚአብሔር የበጎ ኅሊና ልመና ነው</u> እንጂ፤ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው።» (1ጴጥ. 3፥20-21)

ይህ ጥቅስ ጥምቀት ያድናል አይልም፤ ነገር ግን «የመዳናችን <u>ምሳሌ»</u> ነው። ይህ የውሃ ጥምቀት፣ የጥምቀት ዐይነቶችን ስንዘረዝር በተራ ቍጥር አንድ ላይ የተመለከተው መንፈስ ቅዱስ በክርስቶስ አካል ውስጥ

ሲያጠምቀን የዳንንበት ጥምቀት ምሳሌ ነው። «ይህም ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት <u>ምሳሌው</u> ሆኖ አሁን ያድነናል» የሚለው ስለዚህ ነው። በተራ ቍጥር አንድ ላይ የተገለጸው ጥምቀት፣ በማይታየው ዓለም በመንፈስ የሚከናወን ሲሆን፣ ይህኛው የውሃ ጥምቀት ደግሞ በሚታየው ዓለም የሚፈጸምና በማይታየው ዓለም ለተከናወነው ጥምቀት ምሳሌ የሚሆን ነው። ስለዚህ እውነተኛውን አካል ከጥላውና ከምሳሌው መለየት አለብን። የሚያድነን የውሃው ጥምቀት ሳይሆን፣ የውሃው ጥምቀት ምሳሌ የሆነው ነገር ነው።

| የጥምቀቱ ዐይነት | አጥማቂው | በምን ውስጥ? | ለምን? | ጥቅሶች |
|---|---|---|---|---|
| አንዲቷ ጥምቀት | መንፈስ ቅዱስ | በክርስቶስ አካል | ለደኅንነት (ዐዲስ ፍጥረት ለመሆን) | 1ቆሮ. 12፣13፤ ገላ. 3፥27፤ ኤፌ. 4፥4-5 2ቆሮ. 5፥17 |
| የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት | መጥምቁ ዮሐንስ | በውሃ | ለንስሓ | ሉቃ. 3፥3 |
| የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት | ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ | በመንፈስ ቅዱስ | ኀይልን ለመቀበልና ምስክር ለመሆን | ሐዋ. 1፥5ና 8 ማቴ. 3፥11 |
| የመከራ ጥምቀት | ዓለምና ጠላት | በመከራ | የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን እንዲፈጸም | ሉቃ.12፥50 ማቴ. 20፥22፤ ሉቃ. 22፥42፤ 1ጴጥ. 4፥19 |
| ለአማኝ የታዘዘው የውሃ ጥምቀት | የእግዚአብሔር አገልጋይ | በውሃ | ከክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ጋር ለመተባበር (ለክርስቶስ ያለንን ምስክርነታችንንና መታዘዛችንን ያሳያል) | ማቴ. 28፥19፤ ማር. 16፥16 |

ሐ. <u>ይህ ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ «ጽድቅ» ብሎ የጠራው ሥርዐት ነው</u>፡፡

«ኢየሱስም መልሶ፤ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው፡፡ ያን ጊዜ ፈቀደለት፡፡ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውሃ ወጣ፡፡» (ማቴ. 3፥15-16)

ጽድቅ ብሎ የተናገረው የሚያድነን ሥርዐት ነው ለማለት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሥርዐት ነው ለማለት ነው፡፡ አንድ ሕግ ጸደቀ ሲባል «ተቀባይነት አገኘ» ማለት እንደ መሆኑ መጠን ይህንንም ሥርዐት ስንፈጽም፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ነገር አደረግን ማለት ነው፡፡

## <u>ጥምቀት ከእምነት በኋላ እንጂ ከእምነት በፊት የሚፈጸም ሥርዐት አይደለም</u>

የእግዚአብሔርን ቃል ስንመረምር አንድም ቦታ ሰዎች ከማመናቸው በፊት ሲጠመቁ አናይም፡፡ የተጠመቁትን ሰዎች ሁሉ ስናይ፣ የተጠመቁት ካመኑ በኋላ ነበረ፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን በሐዋ. ምዕ. 8 ላይ የምናገኘው ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ነው፡፡

«በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውሃ ደረሱ፤ ጃንደረባውም እነሆ፣ ውሃ እንዳልጠመቅ የሚከለክለኝ ምንድን ነው? አለው፡፡ ፊልጶስም፡- <u>በፍጹም ልብህ ብታምን፣ ተፈቅዶአል</u> አለው፡፡ መልሶም፡- ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ፡፡ ሠረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፤ ፊልጶስና ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውሃ ወረዱ፤ አጠመቀውም፡፡» (ሐዋ. 8፥36-38)

«የምኵራብ አለቃ ቀርስጶስም ከቤተ ሰዎቹ ጋር በጌታ አመነ፤ ከቆሮንቶስ ሰዎችም ብዙ <u>አምነው ተጠመቁ</u>፡፡» (ሐዋ. 18፥8)
<u>ያመነ የተጠመቀም</u> ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል፡፡» (ማር. 16፥16)
«ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊልጶስን <u>ባመኑት ጊዜ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ፤ ሲሞንም ደግሞ ራሱ አመነ፤ ተጠምቆም</u> ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር፡፡» (ሐዋ. 8፥12-13)

ከእነዚህ ጥቅሶች ሁሉ የምንረዳው፣ ጥምቀት አንድ ሰው <u>ካመነ በኋላ</u> የሚፈጸም ሥርዐት እንጂ ከእምነት በፊት የሚደረግ ሥርዐት አለመሆኑን ነው፡፡ ሰዎች በመጀመሪያ ተጠምቀው በኋላ አመኑ የሚል ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ አንድም ቦታ አናይም፡፡ ምሳሌያችን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ በዘፀአት 13፥2 «ማሕፀንን የሚከፍት በኵርን ሁሉ ለእኔ ቀድስልኝ፤ የእኔ ነው፡፡» በሚለው ቃል መሠረት በሕፃንነቱ በጌታ ፊት ሊያቆሙት ማርያምና ዮሴፍ ወደ መቅደስ ወስደውት እንደ ነበረ በሉቃስ 2፥22-24 እናነባለን፡፡ የተጠመቀው ግን በ30 ዓመቱ እንደ ነበረ የእግዚአብሔር ቃል በሉቃስ 3፥21-23 ይነግረናል፡፡





## <u>የውሃ ጥምቀት አፈጻጸም</u>

አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የተለያየ ዐይነት የውሃ ጥምቀት አፈጻጸም እንዳላቸው ብናውቅም፣ በእግዚአብሔር ቃል ስለ ጥምቀት አፈጻጸም ይናገራል ብለን የምናምነውን በዚህ ክፍል እናሰፍራለን፡፡ የጥምቀት ሥርዐት አፈጻጸም ልዩነት በክርስቲያኖች መካከል የመለያየት ምክንያት መሆን እንደሌለበት እናምናለን፤ ምክንያቱም አንድነታችን የተመሠረተው በጌታችንና በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ባለን መሠረታዊ እምነት እንጂ በየትኛውም ዐይነት መንገድ የጥምቀትን ሥርዐት በመፈጸማችን አይደለም፡፡ ከጥምቀት ዐይነቶች ውስጥ በተራ ቍጥር አንድ ላይ በጠቀስነው መሠረት በክርስቶስ አካል ውስጥ እስከ ተጠመቅን ድረስ፣ አንድ የሚያደርገን ያ ነው፡፡ ሆኖም፤ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ስለ ጥምቀት አፈጻጸም ይናገራል ብለን የምናምነውን በዚህ ክፍል እንጠቅሳለን፡፡

ሀ.የውሃ ጥምቀት ሙሉ ለሙሉ በውሃ ውስጥ በመግባት የሚፈጸም ሥርዐት ነው፡፡ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት በማቴ. 3፥13-17 ስንመለከት፣ «ኢየሱስ ተጠምቆ <u>ከውሃ እንደ ወጣ</u> ...» የሚል ቃል እናነባለን፡፡ በሐዋ 8፥36ም ስለ ፊልጶስና ስለ ኢትዮጵያዊው ጃንደረባ ሲናገር፣ «ሁለቱም <u>ወደ ውሃ ወረዱ</u>...» የሚለውን እናገኛለን፡፡ ዐዲስ ኪዳን በመጀመሪያ በተጻፈበት በግሪክ ቋንቋ «ጥምቀት» የሚለው ቃል ወደ አንድ ነገር ውስጥ መግባትን ወይም መጥለቅን ያመለክታል፡፡

ለ. ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴ. 28፥19 በሰጠን መመሪያ መሠረት የምንጠመቀው «በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም» ነው፡፡ አንዳንድ በሥላሴ የማያምኑ ክርስቲያኖች፣ መጠመቅ ያለብን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ሳይሆን፣ በኢየሱስ ስም ብቻ ነው በማለት ያስተምራሉ፡፡ ይህንንም ለመደገፍ የሚጠቀሙበት ማስረጃ በሐዋ. ሥራ ውስጥ ሐዋርያት በኢየሱስ ስም ማጥመቃቸውን በመጥቀስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር ቃል እርስ በእርሱ ስለማይቃረን ሐዋርያት በኢየሱስ ስም ያጠመቁበትን ምክንያት ማስተዋል አለብን እንጂ፣ ኢየሱስ የሰጠንን ግልጽ የሆነ ትእዛዝ ችላ ማለት የለብንም፡፡ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችበት ዘመን የኢየሱስ ስምና የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት የተጠሉበትና የሚሰደዱበት ዘመን ስለ ነበረ፣ በዚያን ጊዜ አንድ ሰው በእውነት በኢየሱስ ክርስቶስ ማመኑን የሚያረጋግጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በመጠመቅ ነበረ፡፡ ሐዋርያት ያንን ለማረጋገጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ያጠምቁ ነበር፡፡ ነገር ግን ለትውልድ ሁሉ የተሰጠው መመሪያ «<u>በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም</u>» እንድንጠመቅ ነው፡፡

## <u>ስለ ጥምቀት ሁለት የተዛቡ አመለካከቶች</u>

ሀ. ያለ ጥምቀት አንድ ሰው መዳን አይችልም የሚል የተሳሳተ እምነት አለ፡፡ ይህንን እምነት የሚከተሉ ክርስቲያኖች የሚጠቅሷቸው የተለያዩ ጥቅሶች አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹን ቀጥሎ እንጠቅሳለን፡፡

ማር. 16÷16 «ያመነ የተጠመቀም ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።» ይህ ጥቅስ «ያመነ የተጠመቀም» ይድናል ይላል እንጂ «ያመነ ነገር ግን ያልተጠመቀ» አይድንም አይልም፤ ወይም «ያላመነ ይፈረድበታል» ይላል እንጂ «ያላመነ ወይም ያልተጠመቀ» ይፈረድበታል አይልም። ማንኛውንም ጥቅስ ከሚናገረው ዐልፈን ልንተረጉመው አንችልም።

1ጴጥ. 3÷20-21፣ «ጥቂቶች ማለት ስምንት ነፍስ በውሃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ፣ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ ዘመን በቈየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዙም። ይህም ውሃ ማለት ጥምቀት <u>ምሳሌው ሆኖ</u> አሁን ያድነናል፤ የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም፤ ለእግዚአብሔር የበጎ ኅሊና ልመና ነው እንጂ፤ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው» ይላል። ስለዚህ ጥቅስ ቀደም ብለን በቂ ማስረጃ ስለ ሰጠን፣ ማብራሪያውን አንደግምም።

ዮሐ. 3÷5፣ «ሰው ከውሃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።» ይህንን ጥቅስ አንድ ሰው በውሃ ውስጥ ካልተጠመቀና በመንፈስ ቅዱስ ካልተሞላ መዳን አይችልም እንደሚል አድርገው የሚተረጉሙት ሰዎች አሉ። ነገር ግን በ1ጴጥ. 1÷23 ላይ፣ «<u>ዳግመኛ የተወለዳችሁት</u> ከሚጠፋ ዘር አይደለም፤ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።» የሚል ቃል እናነባለን። የእግዚአብሔርን ቃል የምንተረጉመው በራሱ በእግዚአብሔር ቃል ስለ ሆነ፣ በዮሐ 3÷5 ላይ ውሃ የሚለው የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ሆነ መረዳት እንችላለን። አንድ ኀጢአተኛ ሕያው የሆነውን የእግዚአብሔርን ቃል በሚሰማበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ያንን ሕያው ቃል በመጠቀም ያንን ኀጢአተኛ ሰው በመውቀሥና ወደ ንስሓ በማምጣት በክርስቶስ አካል ውስጥ ያጠምቀዋል። በዚህ ጥቅስ ላይ «ከውሃና ከመንፈስ» ሲል ይህንን ማለቱ ነው። በተጨማሪም በኤፌ. 5÷26 ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ከውሃ ጋር ሲያመሳስለው እናያለን። «<u>በውሃ መታጠብና ከቃሉ</u> ጋር አንጽቶ እንዲቀድሳት ስለ እርስዋ (ስለ ቤተ ክርስቲያን - ስለ አካሉ) ራሱን አሳልፎ ሰጠ።» በዐዲሱ፣ ትርጕም ደግሞ «የቀደሳትም» በቃሉ አማካይነት <u>በቃሉ አጥቦ</u> ነው» ይላል።

ሐዋ 2÷38 «ንስሓ ግቡ፤ ኀጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።» በተለይ ይህ ጥቅስ፣ ጥምቀት ለኀጢአት ስርየት የግድ ያስፈልጋል ለማለት የሚጠቀሙበት ጥቅስ ነው። የእግዚአብሔር ቃል፣ «ቃሉ በሙላት ይኑርባችሁ» ስለሚል፣ አንድ ጥቅስ ብቻ ይዘን ድምዳሜ ላይ መድረስ በጣም አደገኛ ነው። የእግዚአብሔር ቃል በአጠቃላይ ስለ «ኀጢአት ስርየት» ምን ይላል? ብለን መጠየቅና መረዳት አለብን።





<u>የእግዚአብሔር ቃል ስለ ኀጢአት ስርየት ምን ይላል?</u>

<u>«ኀጢአታችሁ ይደመሰስ (ይሰረይ) ዘንድ ንስሓ ግቡ</u>።» (ሐዋ 3÷20)
<u>«በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኀጢአቱን ስርየት እንዲቀበል</u> ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።» (ሐዋ. 10÷43)

<u>«ስለ ብዙዎች የኀጢአት ይቅርታ (ስርየት) የሚፈስ የዐዲስ ኪዳን ደሜ</u> ይህ ነው።» (ማቴ. 26÷28)
«እርሱንም (ክርስቶስን) እግዚአብሔር <u>በእምነት</u> <u>የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስረያ</u> አድርጎ አቆመው።» (ሮሜ 3÷25)

እነዚህን ጥቅሶች በደንብ አስተውለን ካነበብን፣ አንዳቸውም የኀጢአት ስርየት በጥምቀት ይገኛል አይሉም፤ ነገር ግን ስለ ኀጢአታችን ስርየት ስለ ፈሰሰው <u>ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ደምና ስም</u>፣ <u>ንስሓ ስለ መግባትና</u> በእርሱ ስለ ማመን ብቻ ነው የሚናገሩት። በዐጭሩ አንድ ኀጢአተኛ በኀጢአቱ ተናዝዞ፣ በክርስቶስ በሚያምንበት ጊዜ፣ «<u>የኀጢአቱን ስርየት እንዲቀበል</u> ነቢያት ሁሉ ይመሰክሩለታል።» ኀጢአቱን ሁሉ የሚያስተሰርይ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ፈሶለታልና።

ለ. ሌላው የተዛባ አመለካከት ደግሞ ጥምቀትን ችላ በማለት እንደ ተራ ነገር መቍጠር ነው።

ለዚህ ዐይነቱ አመለካከት አንድ ጥያቄ ብቻ ጠቅሶ ማለፉ በቂ ይሆናል። ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ «ጽድቅን ሁሉ ልንፈጽም ይገባናል» ብሎ ከተጠመቀ እኛ እንዴት የጥምቀትን ሥርዐት ቸል እንላለን?

<u>በአጠቃላይ በዚህ ክፍል ስለ ጥምቀት የተማርነው፦</u>

1. ጥምቀት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱ «ጽድቅ» ብሎ የጠራው ሥርዐት እንደ ሆነ፣
2. ጥምቀት ከእምነት በኋላ እንጂ ከእምነት በፊት የሚፈጸም እንዳልሆነ፣
3. ጥምቀት <u>ስለ ዳንን</u> እንጂ <u>ለመዳን</u> የምንፈጽመው ሥርዐት እንዳልሆነ፣
4. ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር አንድ መሆናችንን የምንመሰክርበት መንገድ እንደ ሆነ።
5. ለእግዚአብሔር ያለንን መታዘዝና መሰጠት የሚያሳይ እንደ ሆነ።

እንደ ዳዊት እኛም እንዲህ እንበል፤
«የሥርዐትህን መንገድ እንዳስተውል አድርገኝ።»
መዝ. 118 (119)÷27።

## ትምህርት ሰባት፡- የቤተ ክርስቲያን ሥርዐቶች

የመታወቂያ ቊጥር፤ ____________________

ስም፤ ____________________

አድራሻ፤ ____________________

____________________

____________________

1. የቅዱስ ቊርባን ሥርዐት እንዴት (ለምን) ተጀመረ?
2. ቅዱስ ቊርባን ምንንና ምንን ያጠቃልላል? እያንዳንዱስ የሚያመለክተው ምንድን ነው?
3. ቅዱስ ቊርባን መቀበል ያለበት በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ዳግመኛ የተወለደ ሰው ነው፡፡ እንደ አማኝ ቅዱስ ቊርባን ከመቀበልህ በፊት ምን ማድረግ አለብህ?
4. አንድ አማኝ በውሃ ሲጠመቅ የሚያስተላልፈው መልእክት ምንድን ነው?
5. አንድ ሰው የሚጠመቀው ደኅንነትን ለማግኘት ነው ወይስ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ከዳነ በኋላ ነው?
6. ኢየሱስ ከመጠመቁ በፊት መጥምቁ ዮሐንስ፣ «አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና፡፡» ሲል ምን ማለቱ ነው?
7. ከጥምቀት ዐይነቶች ውስጥ በተራ ቊጥር 1እና 5 መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ፡፡
8. የጥምቀትን ሥርዐት ፈጽመሃል?
   መልስህ ፈጽሜአለሁ ከሆነ፣ የፈጸምኸው ከማመንህ በፊት ነው ወይስ ካመንህ በኋላ?
   መልስህ አልፈጸምሁም ከሆነ፣ ወደፊት ለመጠመቅ ዕቅድ አለህ?